በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ደስ የምናሰኘው ማንን ነው?


**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ነሐሴ ፲ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም.**

# ደስ የምናሰኘው ማንን ነው?

1. <u>መግቢያ</u>

- በዚህ ዓለም በሦስት መንገድ የሚደሰቱ ወይም የሚያስደስቱ ሰዎች አሉ። እነርሱም ራሳቸውን የሚያስደስቱ፣ ሰዎችን ደስ የሚያሰኙ እና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ በመባል ይታወቃሉ።
- ዘወትር በሕይወታችንም ሆነ በአገልግሎታችን ማንን ደስ ለማሰኘት እንደምንሞክር መገምገም ያስፈልገናል። በክርስትና ሕይወትም ሆነ በክርስቲያናዊ አገልግሎት ራስን ወይም ሰውን ደስ የምናሰኝ ሆነን መገኘት አደገኛ ምልክት ነውና። ይልቁንም በዚህ ሕይወት የሚመላለስ አገልጋይ ለሌሎች መንፈሳዊ ሕይወት ታላቅ የመሰናክል ደንጊያ ነው።
- እንዲህ ያለውም አማኒ ወይም አገልጋይ በከፍተኛ የመንፈሳዊ ሕይወት ውድቀት ክልል ውስጥ የሚገኝ ከመሆኑ ባሻገር ሰውን ወይም ራሱን ደስ ለማሰኘት ሲል የተከተለው አቅጣጫ የተደረገለትንም መዳን እስከማጣት ሊያደርሰው ይችላል።
- በክርስትናችን የነገሮች ሁሉ ዋናው ግብ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት ነው። ይህም የሚገኘው በእምነታችን፣ በአምልኮታችንም ሆነ በአገልግሎታችን በእውነት እግዚአብሔርን ለማክበር (ክብሩን ለመግለጥ) ስንፈልግና ደስ ልናሰኘውም ስንጣጣር ነው።

2. <u>ራሳቸውን ደስ የሚያሰኙ ሰዎች</u>

- ራሳቸውን ደስ ለማሰኘት ቅድሚያ የሚሰጡ ሰዎች ራስ ወዳዶች ናቸው። ነገሮችን ሁሉ የሚያደርጉት ራሳቸውን ለማክበርና ደስ ለማሰኘት ብቻ ነው። ለዚህም የሚያነሳሳቸው ክብራቸውን መፈለግ፣ ራስን ማጽደቅ፣ ታዋቂነትን ወይም ዝናን መሻትና የራስ ስብእናን ብቻ መገንባት ነው።

# ደስ የምናሰኘው ማንን ነው?

2. ***ራሳቸውን ደስ የሚያሰኙ ሰዎች…***

- **በዚህ ሕይወት ከተገኘን የሚከተሉት ምልክቶች ግልጥ ሆነው ይታዩብናል፡-**
  - ***ራሳችንን መውደድ፡-*** **ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይኽን አስመልክቶ ስለ መጨረሻው ቀናት በጻፈው መልእክቱ** ‹‹ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፥ ገንዘብን የሚወዱ፥ ትምክህተኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያመሰግኑ፥ ቅድስና የሌላቸው፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ዕርቅን የማይሰሙ፥ ሐሜተኞች፥ ራሳቸውን የማይገዙ፥ ጨካኞች፥ መልካም የሆነውን የማይወዱ፥ ከዳተኞች፥ ችኩሎች፥ በትዕቢት የተነፉ፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤ የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፤ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ።›› ***ካል ጢሞ 3፡2-5*** **እንዳለን ሆነን እንገኛለን፡፡**
  - ***ራሳችንን ደስ ማሰኘት፡-*** ‹‹ እኛም ኃይለኞች የሆንን የደካሞችን ድካም እንድንሸከም ራሳችንንም ደስ እንዳናሰኝ ይገባናል።›› ***ሮሜ 15፡1***
  - ***የራሳችንን ትርፍ መፈለግ፡-*** ‹‹እኔ ደግሞ ብዙዎቹ ይድኑ ዘንድ ለጥቅማቸው እንጂ የራሴን ጥቅም ሳልፈልግ በሁሉ ነገር ሰውን ሁሉ ደስ እንደማሰኝ እናንተም እንዲሁ ሁኑ፥ ለአይሁድም ለግሪክም ሰዎች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም ማሰናከያ አትሁኑ።›› ***ቀዳ ቆሮ 10፡33፡፡*** ‹‹ሁሉ የራሳቸውን ይፈልጋሉና፥ የክርስቶስ ኢየሱስን አይደለም።›› ***ፊል 2፡21፡፡***
  - ***ከጥቅም ኋላ መሮጥ፡-*** ‹‹መብል ወዳጆች ከቶ የማይጠግቡ ውሾች ናቸው፥ እነርሱም ያስተውሉ ዘንድ የማይችሉ እረኞች ናቸው ሁሉ ወደ መንገዳቸው፥ ከፊተኛው እስከ ኋለኛው ድረስ ሁሉ፥ እያንዳንዳቸው ወደ ጥቅማቸው ዘወር ብለዋል።›› ***ኢሳ 56፡11፡፡***

# ደስ የምናሰኘው ማንን ነው?

2. **_ራሳቸውን ደስ የሚያሰኙ ሰዎች…_**

- **በዚህ ሕይወት ከተገኘን የሚከተሉት ምልክቶች ግልጥ ሆነው ይታዩብናል፦**
    - **_ክብርን መፈለግ፦_** ‹‹እርሱም፦ ምን ትፈልጊያለሽ? አላት። እርስዋም፦ እነዚህ ሁለቱ ልጆቼ አንዱ በቀኝህ አንዱም በግራህ በመንግሥትህ እንዲቀመጡ እዘዝ አለችው።›› **_ማቴ 20፡21፡፡_** እንደተባለ፡፡
    - **_ለራሳችን ብቻ መኖር፦_** ‹‹በሕይወትም ያሉት ስለ እነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደ ፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ስለ ሁሉ ሞተ።›› **_ካል ቆሮ 5፡15፡፡_**
    - **_ድሆችን መርሳት፦_** ‹‹ነገር ግን የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው፥ ወንድሙም የሚያስፈልገው ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን፥ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል?›› **_ቀዳ ዮሐ 3፡17፡፡_**
    - **_እግዚአብሔርን ለሚጠፋ ጥቅምና ሽልማት ሲሉ ማገልገል፦_** ‹‹ በመሠዊያዬ ላይ እሳትን በከንቱ እንዳታቃጥሉ ከእናንተ ዘንድ ደጅ የሚዘጋ ሰው ምነው በተገኘ! በእናንተ ደስ አይለኝም፥ ቍርባንንም ከእጃችሁ አልቀበልም፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡፡›› **_ሚል 1፡10፡፡_**
    - **_ግዳጃችንን ለሚጠፋው ጥቅማችን ስንል መወጣት፦_** ‹‹አለቆችዋ በጉቦ ይፈርዳሉ፥ ካህናቶችዋም በዋጋ ያስተምራሉ፥ ነቢያቶችዋም በገንዘብ ያምዋርታሉ ከዚህም ጋር። እግዚአብሔር በመካከላችን አይደለምን? ክፉ ነገር ምንም አይመጣብንም እያሉ በእግዚአብሔር ይታመናሉ።›› **_ሚክ 3፡11፡፡_**
- **ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙትን አስመልክቶ** ‹‹ በክርስቶስም አንዳች ምክር ቢሆን፥ የፍቅር መጽናናት ቢሆን፥ የመንፈስ ኅብረት ቢሆን፥ ምሕረትና ርኅራኄ ቢሆኑ፥ ደስታዬን ፈጽሙልኝ፤ በአንድ አሳብ ተስማሙ፥ አንድ ፍቅር አንድም ልብ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ፤ ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር፤ እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፥ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ።›› **_ፊል 2፡1-4፡፡_** **በማለት እንዲህ ያለው ክርስቲያናዊ ሕይወትና አገልግሎትም ሰማያዊ እንደሆነ አረጋግጦልን በዚህኛው መንገድ ጸንተን እንድንራመድ መክሮናል፡፡**

# ደስ የምናሰኘው ማንን ነው?

## 3. ሰዎችን ደስ የሚያሰኙ ሰዎች

- **ሰዎችን ደስ ማሰኘት ከሁሉ በላይ አደገኛ ነውርና ድካም ውስጥ የሚጥለን ከመሆኑም በላይ አማንያንም ሆኑ አገልጋዮች ሳያስተውሉት ወይም ችግራቸውን ለይተው ከመንፈሳዊው አቅጣጫ ለቀው መውጣታቸውን ሳያውቁት ለሚመላለሱበት አደገኛ ሕይወት የሚዳርግ ነቀርሳ ነው፡፡**
- **ቅዱስ ጳውሎስ** ‹‹ባሪያዎች ሆይ፥ ለክርስቶስ እንደምትታዘዙ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ በልባችሁ ቅንነት በሥጋ ጌቶቻችሁ ለሆኑ ታዘዙ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚያደርጉ እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች እንጂ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ ትሁኑ። ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምትገዙ በትጋትና በበጎ ፈቃድ ተገዙ፤ ባሪያ ቢሆን ወይም ጨዋ ሰው፥ እያንዳንዱ የሚያደርገውን መልካም ነገር ሁሉ ከጌታ በብድራት እንዲቀበለው ታውቃላችሁና። እናንተም ጌቶች ሆይ፥ ዛቻውን ትታችሁ እንዲሁ አድርጉላቸው ፥ በእነርሱና በእናንተ ላይ የሚገዛው ጌታ በሰማይ እንዳለ ለሰው ፊትም እንዳያደላ ታውቃላችሁና።›› ***ኤፌ 6፡5-9፡፡*** **ብሎናል፡፡**
- **እንዲሁም** ‹‹ባሪያዎች ሆይ፥ በቅን ልብ ጌታን እየፈራችሁ እንጂ፥ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ ሳትሆኑ፥ በሥጋ ጌቶቻችሁ ለሆኑ በሁሉ ታዘዙ።›› ***ቆላ 3፡22***፣ ‹‹ሰውን ወይስ እግዚአብሔርን አሁን እሺ አሰኛለሁን? ወይም ሰውን ደስ ላሰኝ እፈልጋለሁን? አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንሁም።›› ***ገላ 1፡10*** **በማለትም የተመከርነው ለዚሁ ነው፡፡**

**ሰዎችን ደስ የሚያሰኙ ሰዎች መታወቂያ ምልክቶች፡-**

- ***ከእግዚአብሔር ይልቅ የሰውን ማረጋገጫ ይፈልጋሉ***
  - **ሰዎች የባልጀሮቻቸውን ሙገሳና አድናቆት የሚያስተናግዱበት ወይም የሚቀበሉበት ዝንባሌ ያሳያሉ፡፡ መወደስና መከበርን ስለሚሹ፣ በዚህም ችግር ስለሚመረዙና አስፈላጊ ነገር እንደሆነ ወደ መቁጠር ስለሚገቡ የሰውን አድናቆት ተስፋ ሲያደርጉ ይገኛሉ፡፡**

# ደስ የምናሰኘው ማንን ነው?

## 3. ሰዎችን ደስ የሚያሰኙ ሰዎች…

**ሰዎችን ደስ የሚያሰኙ ሰዎች መታወቂያ ምልክቶች…**

- ***ከእግዚአብሔር ይልቅ የሰውን ማረጋገጫ ይፈልጋሉ…***
    - የዚህም ሞራላዊ ክስረት ቀጣይ እርምጃ እንደ ሰው በማንኛውም ጉዳይ ከሁሉ አስቀድመው ከሰው ማረጋገጫን መፈለግ ነው፡፡ ጌታችን በመዋዕለ ሥጋዌው ***በማቴ 6*** የወቀሳቸው ሰዎች ከእነዚህ ወገን ናቸው፤ ‹‹በሰው ዘንድ ሊከበሩ በምኩራብ በመንገድም ምጽዋታቸውን ይሰጡ፣ መለከት ያስነፉም ነበር፡፡››
    - ይህን መሰል ደካማነት ሲጾሙም ሆነ ሲጸልዩ ያሳዩ ነበር፡፡ የሕዝብ መሪዎች ከነበሩ ፈሪሳውያንም የክርስቶስን ሰው መሆን ለመረዳት የሚችሉበት ትምህርት ቢኖራቸውም ‹‹ነገር ግን ከምኵራብ እንዳያስወጡአቸው በፈሪሳውያን ምክንያት አልመሰከሩለትም፤ ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ የሰውን ክብር ወደዋልና።›› ***ዮሐ 12፡41፡፡***
    - ጌታችን ‹‹ ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሩላችሁ፥ ወዮላችሁ፤ አባቶቻቸው ለሐሰተኞች ነቢያት እንዲሁ ያደርጉላቸው ነበርና። ›› ***ሉቃ 6፡26፡፡*** በማለት የችግሩ ምንነት ተነግሮናል፡፡
    - የሰዎች ምላሽ ምንም ይሁን ምን የእግዚአብሔር ልጆች ከሁሉ አስቀድመን ስለምንሠራው ሥራም ሆነ ስለምንሰጠው አገልግሎት የእግዚአብሔርን ማረጋገጫ መፈለግ አለብን፡፡
- ***ሥልጣን መቆናጠጥን፣ በማኅበራዊ ሕይወት ከፍ ማለትን፣ በክብር መግነን ይፈልጋሉ***
    - ሰዎችን ደስ የሚያሰኙ ሰዎች ዋነኛ መታወቂያቸው የሥልጣን ጥመኞች፣ በማሕበራዊ ሕይወት ከፍታን ወዳጆች፣ ክብርን ፈላጊዎች መሆናቸው ነው፤ ይህን ለማሳካትም በማንኛውም ነገር ላይ ይንጠላጠላሉ፤ በዚህም የሚፈልጉትን ለመቆናጠጥ ሰዎችን አስደሳች ብቻ ይሆናሉ፡፡

# ደስ የምናሰኘው ማንን ነው?

3. **ሰዎችን ደስ የሚያሰኙ ሰዎች...**

**ሰዎችን ደስ የሚያሰኙ ሰዎች መታወቂያ ምልክቶች...**

- ***ሥልጣን መቆናጠጥን፣ በማኅበራዊ ሕይወት ከፍ ማለትን፣ በክብር መግነን ይፈልጋሉ***
  - እንዲህ ያሉ ሰዎችን ለማስደሰት የተሰለፉ ሰዎች ከፍ ባለ ወጥመድ ውስጥ ራሳቸውን ይጥላሉ። ከእውነት ፈቀቅ ይላሉ፣ ከጀርባ ሆነው ይናገራሉ፣ ሐሜተኞች ናቸው፣ ይሳደባሉ፣ ሌሎችን ለማስደሰት ሲሉ ማንኛውንም ነገር ያደርጋሉ፤ ይህንም ሥልጣን ለመቆናጠጥ፣ ቦታ ለመያዝና ማኅበራዊ ሥፍራ ለማግኘት ይጠቀሙበታል።
  - እንዲህ ላሉ ሰዎች የመዳናቸው ነገር ቀዳሚ ጉዳይ አይደለም፤ የሚያድጉትም የዚህን ዓለም ነገር ለመውደድ ነው። ለመንፈሳዊውም ነገር እውራን ይሆናሉ።
  - ክርስቲያኖች እንዲሁም አገልጋዮች ከዚህ ወጥመድ ስለፍቅር፣ ስለታማኝነትና ስለመከባበር በመናገርና በመቆም ራሳቸውን ነጻ ማውጣት ይጠበቅባቸዋል። ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን ስለ እውነት እንናገር።›› ***ኤፌ 2፡15፡፡*** እንዳለ። ይልቁንም አገልጋዮች እግዚአብሔርን ከሁሉ በማስቀደም ራሳችንን መመርመርና እርሱን ከሰው ሁሉ ማስቀደም ይጠበቅብናል።
  - በመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኘው ሰውን ለማስደሰት ሲሉ የሚሠሩ ሰዎች ምሳሌ የምናደርገው ጴንጤናዊው ጲላጦስ ነው። ጌታችን ምንም እንዳልበደለ ጲላጦስ ቢያውቅም የተጻፈልን የሚነግረን ‹‹ ጲላጦስም የሕዝቡን ፈቃድ ሊያደርግ ወዶ በርባንን ፈታላቸው፥ ኢየሱስንም ገርፎ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጠ።›› ***ማር 15፡15*** የሚለውን ነው።
  - ጲላጦስና ሄሮድስ እንዴት ወዳጆች ሆነው እንደነበር እስኪ አስታውሱ። ጌታችንን ከጲላጦስ ወደ ሄሮድስ እያመላለሱ አንከራተውታል። ‹‹ሄሮድስና ጲላጦስም በዚያን ቀን እርስ በርሳቸው ወዳጆች ሆኑ፥ ቀድሞ በመካከላቸው ጥል ነበረና።›› ***ሉቃ 23፡12፡፡*** እንደተባለ ሰውን ደስ ለማሰኘት የሚጣጣሩ ሰዎች ዓለማዊ ጥቅማቸውን ለማስከበር ሲሉ ከመንገዳቸው ለቀው በመውጣት የጭቃኔን ድርጊት እንደሚፈጽሙ ኢ-ሰብአዊ እንደሚሆኑም ጭምር እናረጋግጣለን።

# ደስ የምናሰኘው ማንን ነው?

## 3. ሰዎችን ደስ የሚያሰኙ ሰዎች...

- ***መልእክታቸውን ሁሉ ለአድማጮቻቸው እንዲመች አድርገው ያስተላልፋሉ***
  - **ሰዎችን ደስ ለማሰኘት የቆረጡ ሰዎች ለሰንበት ት/ቤት ወጣቶች፣ ለአገልጋዮች፣ ለአጃቢዎቻቸው፣ ለመሪዎች፣ ለካህናት፣ ለምዕመናን የሚያስተላልፉት መልእክት ሊስማሙበት የሚችሉት፣ ድካምና ስህተት እንዲታረም ትኩረት ያልተሰጠበት፣ የእግዚአብሔር ፈቃድና ሐሳብ የሌለበት ነው፤ ለነርሱም ይህ ከሁሉ በላይ ነው። በተመሳሳይ ጉዳይ የሚያስተላላፉትንም መልእክት ከአድማጭ አድማጭ ብዙዎችን ለማስደሰት ሲሉ ይለዋውጡታል።**
  - **ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ ጢሞቴዎስ ይህን ለማድረግ ከማይሹ ወገን የሚጠቀሱ ናቸው።** ‹‹ስለዚህ የምወደውንና የታመነውን በጌታ ልጄ የሆነውን ጢሞቴዎስን ልኬላችኋለሁ፥ እኔም በየስፍራው በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንደማስተምር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚሆነውን መንገዴን እርሱ ያሳስባችኋል።›› ***ቀዳ ቆሮ 4:17።***
  - **በእውነተኛ የሃይማኖት ትምህርት ላይ ያልተመሠረቱ ሰዎች ለራሳቸው የሚሆኑ አስተማሪዎችን ያዘጋጃሉ፤ እነዚህም አስተማሪዎች እንደሚስማማቸው አድርገው ይናገሩላቸዋል።** ‹‹በእግዚአብሔር ፊት በሕያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ባለው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት፥ በመገለጡና በመንግሥቱም እመክርሃለሁ፤ ቃሉን ስበክ፥ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና፥ ፈጽመህ እየታገሥህና እያስተማርህ፥ ዝለፍና ገሥጽ ምከርም። ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና፤ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለ ሆነ፥ እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ። እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ፥ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ። አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ፥ መከራን ተቀበል፥ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፥ አገልግሎትህን ፈጽም።›› ***ካል ጢሞ 4:1-5።***
  - **ይህም አካሄድ ንግግራችን ሁሉ ምንም ፍሬ ነገር ወይም የእግዚአብሔር ቃል የሌለበት ዲፕሎማሲያዊ ንግግር ብቻ ወደ መሆን ያድግና እውነትን ቸል ወደ ማለትና ወደ ክህደት ብሎም ኦርቶዶክሳዊ ወዳልሆነ አስተምህሮ ያደርሰናል።**

# ደስ የምናሰኘው ማንን ነው?

3. **ሰዎችን ደስ የሚያሰኙ ሰዎች…**

- ***እውነትን ችላ ይላሉ ይተውታልም***
    - እግዚአብሔር ተከታዮቹም ሆኑ አገልጋዮቹ ‹‹በጊዜውም አለጊዜውም እንዲጸኑ፣ እንዲታገሡ፣ እንዲያስተምሩ ፣ እንዲዘልፉና እንዲገስጹ ይሻል፡፡›› *ካል ጢሞ 4፡2፡፡* ይሁን እንጂ እንዲህ ያሉ ነገሮች ሰውን ለማስደሰት በሚሹ ሰዎች ዘንድ ተፈላጊነት አጥተው፤ እውነትም ወደ ጎን ተገፍታ ከሰው ጓሊና እየተፋቀች ትገኛለች፡፡
    - እውነትን በፍቅር መናገር *ኤፌ 4፡15* አንድ ነገር ቢሆንም ምስጋና ክብርና ከብዙዎች የተሰጠን ከፍ ያለ ዝና ቢሆንም እውነትን አለመናገር ፍቅር ሊሆን እንደማይችል ይዘነጉታል፡፡ አማንያን ሙልጭልጭ መሆን ሲጀምሩ በእውነት ላይ በመረማመድ ሰዎችን ብቻ ለማስደሰት የሚሯሯጡ ይሆናሉ፡፡
- ቀዳማዊና ካልዕ ጢሞቴዎስን እንዲሁም ቲቶን ብናነብ ሰዎችን ደስ ለማሰኘት ከምንደርገው ድካም ተላቀን እግዚአብሔርን ደስ ወደ ማሰኘት ይመሩናል፤ እውነትንም ለመናገር ብቃት ይሰጡናል፡፡

**ማጠቃለያ**

- አማንያንና አገልጋዮች ሁላችን ‹‹ሰውን ደስ ላሰኝ እፈልጋለሁን? ›› *ገላ 1፡10* በማለት ራስን መጠየቅ ያስፈልገናል፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንኩም ነበር፡፡›› እንዳለን ሰውን ደስ የሚያሰኝ ሁሉ የክርስቶስ እውነተኛ ተከታይና አገልጋይ አለመሆኑን በመረዳት የምንሰጠውን ስጦታ፣ የምናቀርበውን አገልግሎት እግዚአብሔር እንዲቀበለን ሆነን እናቅርብ፡፡ ለዚህም የእግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን አማላጅነት አይለየን፡፡ አሜን፡፡

መልካም ሱባኤ
የእመቤታችንን ጣዕሟን ፍቅሯን በረከቷን ያሳድርብን፡፡ አሜን!!!
ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org